የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ
The Holy synod of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church

No 2056/2017
Date 28/2/2010

## ከሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ የወጣ መግለጫ

"በዓለም ካለው ይልቅ ከእናንተ ጋር ያለው ታላቅ ነው።" (1ኛ ዮሐ 4 ፥4)

በስደት ላይ የሚገኘውና በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ 40ኛውን መደበኛ ስብሰባ ከጥቅምት 26-28 /2007 ዓ/ም በኮሎምበስ ኦሐዮ ደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም ካቴድራል አካሂዷል ።

ቅዱስ ሲኖዶሱ በቅዱስነታቸው መልካም ፈቃድ በብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ሰብሳቢነት የተካሄደ ሲሆን ከሁሉ አስቀድሞ ምልዓተ ጉባኤው ስራውን የጀመረው ቅዱስ ፓትርያርኩን በፍጹም ጤንነት ቸሩ አምላካችን እንዲጠብቅልን በጸሎት በማሰብ ነበር። ከዚያ በኋላ ቅዱስ ሲኖዶስ ወቅታዊ በሆኑ ዐበይት ጉዳዮች ላይ ተነጋግሯል ፤ ስለ ሕገ ቤተ ክርስቲያን መከበር ፣ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነጳጳሳት ዘኢትዮጵያን 25ኛ ዓመት በዓለ ሢመትና በዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ የተገዛውን የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት ምረቃ መርሐ ግብር በተመለከተ ፣ ስለ መንበረ ፓትርያርክ ጽሕፈት ቤት መጠናከር ፤ ስለ ስብከተ ወንጌል መስፋፋት ፣ በመካከለኛው ምስራቅ እና በአፍሪካ አክራሪ የእስልምና ኃይሎች በክርስቲያኖች ላይ እየፈጸሙት ስለሚገኘው ኢሰብአዊ የግድያ ተግባር ፣ በሀገራችን ኢትዮጵያ ስለ ሰፈነው ሥርዐት-አልበኝነትና ግፍ ፣ በሌሎችም ዐበይት አገራዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ተወያቶ ከዚህ የሚከተለውን መግለጫ አውጥቷል።

1) ሕገ ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ፦ በውጭ ሀገር የምትገኘውን ቤተ ክርስቲያን በተሻለና በተደራጀ መልኩ ለመምራት ሕገ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም ከዚህ በፊት በቅዱስ ሲኖዶስ ጸድቆ ወደ አድባራት የተላለፈውን ሕገ ቤተ ክርስቲያንና ሌሎችን ቀኖናት ቤተ ክርስቲያን መሠረት አድርጎና ተሻሽሎ የወጣው የተሻሻለው የሕገ ቤተ ክርስቲያን ረቂቅ እርማት ባለመጠናቀቁ ምክንያት ተጨማሪ ሦስት ወራት ለአዘጋጅ ኮሚቴው ተሰጥቶታል። ስለዚህ በሚቀጥሉት ሶስት ወራት ውስጥ ተጠናቆ የቋሚ ሲኖዶስ አባላትና አርቃቂ ኮሚቴው በሎሳንጀለስ ከተማ በጥር ወር ተገናኝተው ኮሚቴው ለቋሚ ሲኖዶስ አባላት እንዲያስረክቡና ቋሚ ሲኖዶስ የተሟላውን ሕገ ቤተ ክርስቲያን አጽድቆ ለአቢያተ ክርስቲያናት ሁሉ ከመሸኛ ደብዳቤ ጋር እንዲላክ እዲያደርግ ቅዱስ ሲኖዶስ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

2) በብጹዕ ወቅዱስ ቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው ቅዱስ ሲኖዶስ ቅዱስነታቸው ለታላቁ የቤተ ክርስቲያን መዓርግ የበቁበትን 25ኛ ዓመት በዓለ ሢመትና በቅርቡ በሜሪ ላንድ እስቴት የገዛውን አዲስ የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት ሕንጻ ምረቃ በዓል ቅዳሜ ኅዳር 13 ቀን 2007 ዓ.ም (Saturday, November 22,2014) ለማክበር በዝግጅት ላይ መሆኑን በመግለጽ ለአብያተ ክርስቲያናት ጥሪ ማስተላለፉ ይታወቃል። ይሁን እንጂ ቅዱስ ሲኖዶስ የዝግጅቱን ይዘት በተመለከተ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት የቀረበውን ሪፖርት መነሻ በማድረግ ሰፊ ውይይት ከአደረገ በኋላ ከላይ በተጠቀሰው ቀን ሊደረግ የታሰበው የበዓል ዝግጅት በሚከተሉት ምክንያቶች ለጊዜው ተላልፎ በግንቦት ወር ከሚደረገው የቅዱስ ሲኖዶስ ዓመታዊ ስብሰባ ጋር ተያይዞ እንዲከበር ውሳኔ አስተላልፎአል። ምክንያቶቹም፦

ሀ) ለዚህ ታሪካዊና ዓለም አቀፍ በዓል የታሰበው ቅድመ ዝግጅት በተለያዩ ምክንያቶች ሙሉ በሙሉ ሊሟላ ስለአልቻለና በቂ የዝግጅት ጊዜ ስለአስፈለገ ፤

ለ) በየዓመቱ በጥቅምት ወር የሚደረገው የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ከቅዱስነታቸው 25ኛ ዓመት በዓለ ሢመትና የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት የምረቃ በዓል ጋር የተቀራረበ በመሆኑ በርካታ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ካህናት በበዓሉ ላይ መገኘት የማይችሉ መሆናቸውን ስለአስታወቁ ፤



4127 Redwood Rd. Oakland CA 94619 Tel: (510) 530 3681

ሐ) በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ በኅዳር ወር የሚከበረው የቅዱስ ሚካኤል አመታዊ በዓል ንግስ ኅዳር 13 ቀን 2007 ዓ.ም. (November 22,2014) የሚከበር በመሆኑ ፤

መ) በግንቦት ወር አዲስ በተገዛው የመንበረ ፓትርያክ ጽ/ቤት ከሚደረገው የቅዱስ ሲኖዶስ(ርክበ ካህናት) ዓመታዊ ስብሰባ ጋር ይህን ታላቅና ታሪካዊ በዓል በአንድ ላይ ቢከበር በቂ የዝግጅት ጊዜ ስለሚሰጥና ሁሉም ሊቃነ ጳጳሳትና ካህናት በበዓሉ ላይ እንዲገኙ ለማድረግ አመቺ መሆኑን ቅዱስ ሲኖዶስ ስላመነበት ነው። በመሆኑም የቅዱስነታቸው 25ኛ ዓመት በዓለ ሢመትና ቅዱስ ሲኖዶስ በቅርቡ የገዛው አዲስ የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት የምረቃ በዓል ለጊዜው እንዲተላለፍና በሚያዚያ 24 ቀን 2007 ዓ.ም በተሻለ ዝግጅት እንዲከበር በቅዱስ ሲኖዶስ የተወሰነ መሆኑን በአክብሮት ያሳውቃል።

3) የዓለምን ሰላምና አንድነት በተመለከተ፦ ዓለማችን በብዙ ማኅበራዊ ፣ኢኮኖሚያዊና ፓለቲካዊ ቀውስ ውስጥ ትገኛለች። በተለይም የሃያማኖት አክራሪነት በአሁኑ ጊዜ ከምንግዜውም በላይ የብዙ ንጹሐን ዜጎችን ሕይወት እያመሳቀለ ይገኛል። ዘመናችን ሃይማኖትን በውል ባልተረዱ በሃይማኖት ስም ተቆርቋሪ ነን የሚሉ አክራሪዎች በፈጠሩት ጥላቻ በየቀኑ የንጹሐን ደም እየፈሰሰ ይገኛል። ለዚህም በመካከለኛው ምስራቅ እስላማዊ መንግሥት እንመሰርታለን ብለው የሚንቀሳቀሱ አክራሪዎች በኢራቅ ፣በሶርያ ፣በአፍሪካና በሌሎችም የዓለማችን ክፍሎች በሚኖሩ ክርስቲያኖችና በልዩ ልዩ ንጹሀን ዜጎች ላይ የሚያደርሱት መከራ ትልቅ ምሳሌ ነው። በዚህ ሰዓት ከሞትና ከስለት የተረፉ በብዙ ሺህ የሚቀጠሩ ክርስቲያኖችም ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል። ሌሎችም በእስር ቤት እየተሰቃዩ ይገኛሉ። ይህንን የመሰለውን ኢሃይማኖታዊ ተግባር ዝም ብሎ ከማየት የከፋ ሃይማኖተቢስነት የለም። በመሆኑም ቅዱስ ሲኖዶስ የንጹሐን ክርስቲያኖችን ደም የሚያፈሱ ነፍሰ ገዳዮችንና ድርጊታቸውን በጽኑ ያወግዛቸዋል። በመከራና በግፍ የሚገኙ ክርስቲያኖችንና ሌሎችንም በጸሎትና በሚያስፈልገው ሁሉ በማገዝ እንደርስላቸው ዘንድ ጥሪውን ያቀርባል።

4) ይህ በዚህ እንዳለ ዓለማችን በአሁኑ ጊዜ እጅግ አደገኛና ገዳይ በሆነ በሽታ በመፈተን ላይ ትገኛለች ፤ ይህ በሽታ ገዳይነቱ ብቻ ሳይሆን ከአንዱ ወደ ሌልላው በፍጥነት ተላላፊ በመሆኑ አንዱ ለአንዱ እንዳያዝንና አንዱ ሌለው እንዳይረዳ በመሆኑ ለሰው ልጆች ከባድ ፈተና ሁኗል። ይህ አደገኛ በሽታ እየተሰፋፋ የሚገኘው በሦስተኛው ዓለም በመሆኑ ደሀው ኅብረተሰብ በዚህ ቀሳፊ በሽታ በመጠቃት ብዙዎች ለሞት ሰለባ ሁነዋል። ስለዚህ ለዓለማችን ከሰማይ አምላክ የታዘዘ ምሕረትና ይቅርታ ያስፈልጋታልና ሁሉም ሕብረተሰብ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር እንዲጮህ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል።

5) ሀገራችን ኢትዮጵያን በተመለከተ፦ ሀገራችን በአሁኑ ጊዜ ከምንጊዜውም በበለጠ በልዩ ልዩ ዘርፈ በዙ ችግሮች ተከባ ትገኛለች። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖቻችን የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ አጥተው በረሀብ ዓለንጋ እየተገረፉ ይገኛሉ። የፖለቲካው አለመረጋጋት በፈጠረው ችግር ምክንያት በብዙ ስውር እስር ቤቶች ውስጥ ንጹሐን ኢትዮጵያውያን እየተሰቃዩ ይገኛሉ። የመጻፍና የመናገር መብት የተነፈጋችው ጸሐፍያን ብዙዎቹ በእሥራት ሌሎችም በፍርሐት ተይዘው እየተሸማቀቁ ይገኛሉ። እንዲሁም ትውልድን ከርስትና ከጉልት በሚነቅለው የገገዙ መደብ አስቸጋሪ የመሬት ይዞታ መመሪያ(ፖሊሲ) ምክንያት ከመኖሪያቸውና ከመሬታቸው ተፈናቅለው መቀመጫና መቆሚያ ያጡ ወገኖቻችን በሀገራቸው ላይ ስደተኞችና መጻተኞች ሁነዋል። በመሆኑም ኢትዮጵያውያንን ከሀገራቸውና ከምድራቸው የሚያሳድደውን ግፈኛ ሥርዓት ፣ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታወግዘዋለች። የናቡቴን ርስት እንደነጠቀው ጨካኝ ንጉሥ እንደ አክአብ የድሆችን ርስት ለመንጠቅ ደማቸውን እያፈሰሰ የአገሩን ዜጎች ርሥትና ምድር የሚነጥቀውን የኢትዮጵያን መንግሥት ኢፍትሐዊ አሰራር እንደ ነቢየ እግዚአብሔር ኤልያስ ታወግዘዋለች።

6) ለጎረቤት ሀገሮች አዋሳኝ የሆነው የሀገራችን ለም መሬት ለሱዳን አሳልፎ በመስጠቱ ምክንያት የተፈናቀሉ ወገኖች በባእዳን ወታደሮች እየተገደሉ እየተሰደዱና ጥቃት እየተፈጸመባቸው ይገኛሉ። በእስር ቤት ያለፍርድ ታስረው የሚንገላቱ ወገኖች ቁጥር ከእዕለት እዕለት እየጨመረ መምጣቱ በሕብረተሰቡ ላይ ፍርሐትና ጭንቀት ስለነገሰበት ሕዝባችን በሀገሩ እንግዳ ለመንግሥቱም ባእድ ሆኗል። በሥልጣን ላይ ያለው አካል ከእስራትና ከሞት ተርፈው ወደ ጎረቤት ሀገር የተሰደዱትን ዜጎችም ወደ ጎረቤት ሀገሮች ሰላዮችን በመላክ ፣ መንግሥት የሀገሪቱን ወሰን በመሸጥ ያፈራውን ወዳጅነት እንደዋጋ በመጠቀም ንጹሐን ዜጎችን መልሶ በመውሰድ ወደማሰቃያ እስር ቤት በመጣል ላይ ነው። በሀገር ውስጥም ሕዝቡን በቋንቋና በጎሳ በመከፋፈል ለትውልድ ከፋፋይና አጥፊ ሥርዓትን በመትከል ላይ ይገኛል። ነገር ግን በዚህ ሰዓት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቅዱስ ሲኖዶስ የሚያስተላልፈው መልክት፦ ገፊዎችም ግፋቸውም ያልፋሉ ፤ አገርና ትውልድ ግን ይቀጥላልና ፣ በፍቅርና በሰላም ፣



4127 Redwood Rd. Oakland CA 94619 Tel: (510) 530 3681

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ

*The Holy synod of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church*

No______________

Date______________

በደምና በአጥንት ተሣስረህ ፣ ጠላትክን በአንድነት እየመከትህ እግዚአብሔርም ግርማና ሞገስ ሁኖህ ብዙ ሽህ ዘመን የአሳለፍህና ከዚህ የደረስከው ሕዝባችን አሁንም አድነትህን ጠብቅ ፣ ለኃላፊው የጎሣና የልዩነት ሥርዓት በመንበርከክ ለልጆችህ የሀፍረትና የሰቀቀን ታሪክን ትተህ እንዳታልፍ ቅዱስ ሲኖዶስ አደራ ይላል። የውጭን ጠላት መክተህ ነጻነትህን ጠበቀህ እንደኖርክ ሁሉ ዛሬም የውስጥ ፈተናና ባለጋራ ሁኖ አንድነትክን እየተፈታነ የሚገኘውን ጸረ-ሃይማትና ጸረ አንድነት ሥርዓት በአንድነት ጸንተህ እድትቋቋመው ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል።

7) በሀገራችን ሰው የገዡን መደብ እስካልደገፈ ድረስ ፤ በሙያውና በኢትዮጵያውነቱ ብቻ ለሀገሩ መንግሥት በነጻነት ለመሥራት አይችልም ፤ ደጋፊ ከሆነ ደግሞ ትምህርትም ሆነ የሙያ ብቃት ባይኖረው ግድ የለውም። እነደነዚህ አይነት ሰዎች መሪ እንዲሆኑ ያደረገው ደግሞ እየአንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ተቓችለው በአንድነት መደራጀት ባለመቻሉ ነው። ስለዚህ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እራሱንና ሀገሩን ከጥቃት ለማዳንና ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያውያን ሁሉ እንድትሆን ለማድረግ ፣ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ለሀገራችሁ በሰላምና በፍቅር አንድ ሁናችሁ ስለሀገራችን ክብርና ስለ ኢትዮጵያዊ ማንነታችን እንድትነሱ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል።

8) የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንንና የአማራውን ሕዝብ ማዳከም ከተቻለም ማጥፋት አላማው እንደ ሆነ በሚነገርለት በኢሀዴግ የግዛት ዘመን የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማች ፤መሪዎች የወያኔ ደጋፊዎችና ካድሪዎች ስለሆኑ በፖለቲካውና በንግዱ ከተሰማራው አካል የበለጠ የሥነ ምግባርና የሞራል ችግር ያለባቸው ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይገኛሉ ። በዚህ ዘመን በመሪነት ላይ የሚቀመጡ በሃማኖት ሰው ስም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወያኔ ያሰማራቸው ሰዎችም መለኪያቸው ፥ ሥነ-ምግባርና እውቀት ሳይሆን የፖለቲካና የቋንቋ ድጋፍ ሁኗል። በመሆኑም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስተዳደራዊ ችግር ተስፋፍቷል። ሀብተ ክህነትና መንፈሳዊ ተልዕኮ በቅድስናና በሁለተናው የቤተ ክርስቲያን ትምህርታዊ የሙያ ብቃት ሳይሆን በሚከፍለው የገንዘብ መጠን የሚወሰን ሁኗል። ይህም ቤተ መግሥቱን ድል ነስቶ ቤተ ክህነቱን የተቆጣጠረው የሙስና ሕይወት ሕዝበ ክርስቲያኑን ስላስመረረው ፣እረኞች የተባሉትም ምንደኞች ስለሆኑ ኢትዮጵያውያን ኦርቶዶክሳውያን ወገኖቻችን እነሱን እያሳየኝ እያሉ ወደ ልዩ ልዩ ሃይማኖት በመፍለስ ላይ ይገኛሉ። ይሁን እንጂ ፤ክርስቲያን ወገኖቻችን ይህ ቀን ያልፋልና የማይለወጠውን አምላካችንን እያመለካችሁ ባለችሁበት ጸንታችሁ እንድትቆሙና ቤተ ክርስቲያናችሁን እንድትጠብቁ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያስተላልፋል።

9) በስደት የሚኖረውን ሕዝብ አንድነት በተመለከተ፦ በዚህ ሰዓት ወደ አምስት ሚልዮን የሚጠጉ ኢትዮጵያውን በመላው ዓለም ተበትነው እንደሚገኙ ይታመናል። እነዚህም ብዙዎቹ ለሀገራቸው በልዩ መንገድ በከፍተኛ ደረጃ ሲያገለግሉ የኖሩ ምሁራንና የስራ ልምድ ያለቸው እንደሆኑ ይታመናል ፤እነዚህ ሁሉ ሀገራቸው ያጣችውን ነጻነት ለመመለስ ሁለተናዊ አስተዋጽኦ ለማድረግ አንድነት ሊኖራቸው ይገባል። በመሆኑም ቅዱስ ሲኖዶስ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በአንድነት ለሀገራቸው እንዲሰሩ ፣ ልዩነቶቻቸውን በመቻቻልና በመነጋገር እንዲያጠቡ ይጠይቃል።

10) የሰው ልጅ የተሰጠውን አእምሮና ነጻነት ተጠቅሞ ስለእውነትና ስለ ፍትህ መቆም ይጠበቅበታል። የራሱን ድርሻ ከተወጣ ከሰው አቅም በላይ የሆነውን ደግሞ በፈጣሪው አጋዠነት ከአሸናፊዎቹ በላይ መሆን ይችላል ፣ ከአሰበውም ይደርሳል ፤ "በዓለም ካለው ይልቅ ከእናንተ ጋር ያለው ታላቅ ነው።" ተብሎ እንደተጻፈ። ስለዚህ የእግዚብሔር ርዳታ ያልታከለበት ነገር ፍሬያማ ስለማይሆን ጸሎተ ምሕላ እንዲደረግ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ወስኗል። በመሆኑም ከመጪው ጾመ ነቢያት ጀምሮ እስከ ልደት ድረስ በእለተ ሰንበት ሕዝበ ክርስቲያኑ ሁሉ በተገኙበት ስለ ሀገር ሰላምና ፍቅር ፣ ስለ ዓለማችን ደኅንነት ፣ በእስር ቤትና በስደት ስቃይ ስለሚደርስባቸው ኢትዮጵያውያን ወገኖች ሁሉ ፣ በመካከለኛው ምስራቅና በአፍሪካ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ታጥቀው የተነሱ ሕፃናትንና እናቶችን በአደባባይ በሰይፍና በጎራዴ በመግደል ላይ ያሉትን ነፍሰ ገዳዮች ስለ ፈሰሰው ንጹሀ ደም እግዚብሔር ፍርድ እዲሰጥ ፣ በዓለም የተበተነውን ሕዝባችንንና አገራችን ኢትዮጵያን እግዚብሔር በረድኤቱ እንዲያስባት በመላው ዓለም ጸሎትና ምህላ ይደረግ ዘንድ ቅዱስ ሲኖዶስ ምህላና ጸሎትን አውጀአል።

11) ለብጹዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትራያሪክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ 25ኛ ዓመት በዓለ ሢመት መታሰቢያና በዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ ለተገዛው የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት የምረቃ በዓል ዝግጅት እርዳታ ለማድረግ ለምትፈልጉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ከዚህ በሚከተለው የቅዱስ ሲኖዶስ የባንክ አካውንት (Bank Of America: Routing # 121000358 (325018014116) በቀጥታ ገቢ በማድረግ ለዚህ ታላቅና ታሪካዊ በዓል ዝግጅት የርዳታ እጃችሁን በመዘርጋት እንድትተባበሩ ቅዱስ ሲኖዶስ በአክብሮት ጥሪ ያቀርባል።



*4127 Redwood Rd. Oakland CA 94619 Tel: (510) 530 3681*

12) እስከዛሬ በተግባር እንዳየነው ወያኔ በአምባ ገነንነት ኢትዮጵያን ከያዘበት ጀምሮ ኢትዮጵያ ሰላምና እርቅ በአባቶች ዘንድ ይገኛል ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ነው። በስደት የሚገኘው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ከሚያልፈው ወያኔ በላይ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነታችን የሚበልጡብን በመሆኑ በሥርዓቱ ክፋት ቀኖና ተጥሶ እንድንከፋፈል የተደረግን አባቶች አንድነታችን ተጠብቆ ክርስቲያናዊ ሀላፊነታችንን እንድንወጣ ዛሬም ለእርቅ እጃችንን ዘርግተን በራችንንም ከፍተን የምንጠባበቅ መሆኑን ለኢትዮጵያ ህዝብ በፅኑ እንገልጻለን።

በመጨረሻም ይህን 40ኛውን መደበኛ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ በማስተናገድ የደከሙትን የኦሐዮ ደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም ካቴድራል ካህናት ፣ ሰበካ ጉባኤ አባላትን እና ምእመናን ቅዱስ ሲኖዶስ ከልብ በማመስገን በብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ ቃለ ምዕዳንና ጸሎተ ቡራኬ ቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤውን አጠናቅቋል።

ስብሐት ለእግዚአብሔር



4127 Redwood Rd. Oakland CA 94619 Tel: (510) 530 3681